የትግራይ ልማት ማሕበር በመቐለ ፣ ማይቐያሕ ፣ ማይቕነጣል ፣ በሰሜን ምዕራባዊ ዞን መደባይ ዛና ወረዳ በዓዲ ባዕራጅ ፣ማይሎሚን ፣ትኩለ ፣ ልምዓት፣ ዛና፣ ኩብርቶ እንዲሁም በማእከላዊ ዞን ላዕላይ ማይጨውና ታሕታይ ማይጨው ወረዳ ደብረ ቃል፣ናትካ ብላዕ፣መደጎይ፣ መሬና፣ ሓውስታና ዓዲ ሑፃ ቀበሌዎች የትምህርትና የጤና ተቋሞች ከሎት1 እስከ ሎት 10 በመከፋፈል / ለሎት 1 ፣2 እና 3 ደረጃቸው GC/BC-4 እና ከዝያ በላይ እንዲሁም ለሎት 4 ፣ 5 ፣ 6 ፣ 7 ፣ 8 ፣ 9 እና 10 ደረጃቸው GC/BC-5 እና ከዝያ በላይ የሆኑ/ ተጫራቾችን ኣወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል

- የተለቀቀበት ቀን: ሰሉስ ታሕሳስ 12, 2008 (ከ 11 ዓመታት)
- መዝግያ ቀን: ጥሪ 1, 2008 6:00 ከሰኣት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:
- ቦታ:መቐለ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:500
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ጥሪ 1, 2008 6:00 ከሰኣት
- ምድብ: ገዛውቲን ሕንፃ ስራሕቲን/

በዚህ መሰረት፦

1. የ2008 ዓ.ም የስራ ግብር የከፈሉ፣የንግድ ስራ ፈቃዳቸው ያሳደሱ፣በኮንስትራክሽን የአቅራቢነት፣የቫት፣ የቲን ሰርትፍኬትና የመጨረሻ ወር የቫት ዲክላሬሽን የሚያቀርቡ፣

2. በትግራይ ክልል ኮንስትራክሽን መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የሚገኝ ዋና የስራ ሂደት ኮንስትራክሽን ቁጥጥርና ፍቃድ የተመዘገቡበት ሰርትፍኬት ወይ ደግሞ ከሌላ ክልል የምዝገባ ሰርተፊኬት ማቅረብ የሚችሉ፣

3. በማንኛውም ቦታ በግንባታ ሂደት ችግር ምክንያት ማስጠንቀቅያ ያልደረሰው ተቋራጭ የሆነ፣

4. የጨረታው ማስከበርያ ዋስትና በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ከተፈቀደላቸው የታወቁ ባንኮች ለGC/BC-5ና ከዝያ በላይ 150,000.00 (ኣንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር) እንዲሁም ለGC /BC-

4ና ከዝያ በላይ 250,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ ብር) በሲፒኦ ብቻ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

5. ተጫራቾች ለሚሰሩት የህንፃ ፕሮጀክት ሳይት ከተረከቡበት ቀን ጀምሮ ለGC/BC-5ና ከዝያ በላይ በ150/ ኣንድ መቶ ሃምሳ ተከታታይ ቀናት እንዲሁም ለGC/BC-4ና ከዝያ በላይ በ210/ ሁለት መቶ ኣስር ተከታታይ ቀናት ኣጠናቆ ማስረከብ የሚችሉ፣

6. የጨረታው ዶክመንት በሪፖርተር ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ21 ተከታታይ ቀናት ኣስፈላጊዉን ዶክመንት በመያዝ የማይመለስ ብር 500 (አምስትመቶ) በመክፈል ከትግራይ ልማት ማህበር ዋና ፅ/ቤት ቢሮ ቁጥር 410 መውሰድ ይችላሉ፣

7. የጨረታው ሰነድ በተጫራቾች መመርያ መሰረት ተሞልቶ ፣ቴክኒካልና ፋይናንሻል ዶክመንቶች ኦርጅናሉና ሁለት ፎቶ ኮፒዎች ፣ ሲፒኦ ለየብቻቸው በሰም ታሽጎው በኣንድ ትልቅ ፖስታ ውስጥ ተከተውና በላዩ ላይ ለሚጫረቱት ፕሮጀክት ስም በሚታይ ቀለም ፅፈው በሁሉም ዶክመንት ላይ ተፈርሞበትና ህጋዊ የሆነ ማህተም በመምታት ይህ ማስታወቅያ ከወጣበት እስከ 21ኛው ቀንና

ከቀኑ 8:30 ሰዓት በትግራይ ልማት ማህበር ዋናው ፅ/ቤት ለዚሁ አገልግሎት የተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፣

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle

8. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸው ባሉበት በ21ኛው ከቀኑ 8.30 የጨረታው ሳጥን ተዘግቶ በዛው ቀን 9:00 በተጠቀሰው ቀንና ቦታ ጨረታው ይከፈታል፣

9. ኣሰሪው ፅ/ቤት የተሻለ መንገድ ካገኘ በጨረታው ኣይገደድም።

10. የመክፈቻው ቀን በዓል ወይም ቅዳሜና እሁድ ከሆና በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል

11. ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር፤-034-440-68-40 መጠየቅ ይቻላል

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle